# « የልጅ ነገር ሁለት ፍሬ፤ አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ »

*አሥራደው (ከፈረንሳይ)*

## ለልጅ ተክሌ :

«እኛ ወያኔዎች (ኢሃአዴግጎች) ጠር መሥራት እንችላለን » ያለን ማን ነበር ? ልጅ ተክሌ : እስቲ ሃሳብ አብላልተህና (አቁላልተህ) አሽትት፤ መጎርናቱ ካልሸተተህ ወይ ሞያ ክደሃል፤ ወይም የማሽተቻ ህዋሶችህ ደንዝዘዋልና የጤና ባለሙያ መጎብኘት ያሻሃል ::

« የትግርኛ ተናጋሪዎች አማርኛ ደስ ይላል እንደወረደ ነው : ቅኔና ተንኮል የለውም »

በአላዋቂዎች መንደር ካልሆነ በስተቀር : ቅኔና ተንኮል ተዳርተው አያውቁም : ቅኔ ቅኔነቱን እንደያዘ በሊቃውንት ሲቀኝ፤ ሲዘረፍ፤ ፍሬ ነገሩ አስተሳሰብን ያሰፋል፤ አይምሮን ያጎለብታል፤ እንጂ አያጠብም : ብዙውን ጊዜ ተንኮል የሚያበዙት : የአስተሳሰብ አድማሳቸው ጠባብና ውሱን : የሆኑ ግለሰቦች ወይም ቡዱኖች ናቸው :: የሚያዳምጡት የራሳቸውን የልብ ትርታ ብቻ በመሆኑ : ጆሯቸውንም አይምሯቸውንም ደፍነው ማንቧረቅ ያዘወትራሉ፤ አይምሯቸውን የሸፈነው ሞራ ሆዳቸውን ከሸፈነው ስለሚልቅ፤ ለምን ? እንዴት ? መቼ ? ማን ? የትቦታ ? ከማንጋር ?....ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎችን አንስተው መማር አይሆንላቸውም : እንዳውም ጩኸታቸው እንደሚባልላቸው ፍርፋሪ ከፍና ዝቅ እያለ የብዙ ሰዎችን የጆሮ ብራና ይጠልዛል እናም ብዙ ሰው ያደነቁራሉ ::

« እነዚህ ሰዎች ደግሞ በቀጣዩ ጥቂት አመታት ውስጥ ስለመወገዳቸው ፍንጭ የሚሰጥ ምንም ነገር የለም .........»

ስለ ቀቢጸ ተስፋነትህ ከራስህ ሌላ የምትወክለው ስለሌለ መብትህ ነው እንዳሻህ:: ሆኖም ያልተገነዘብከው ዛሬ አንተ ላለህበት ትውልድ መሰረት የጣለው « የመሬ ላራሹ » የተማሪዎች መፈክር በስንት ወጣቶች መስዋዕትነት የተዋጀ የድል ውጤት ሲሆን : ባንድ ለሊት ጨረቃ የተሸመጠጠ ሾላ አይደለም :: ዛሬ ወያኔ ገበሬውን ከመሬቱ ነቅሎ ለድንበር ዘለል ዘሪፊ ሲያከፋፍል፤ ወጣቱ እቢኝ ለአገሬ ብሎ የቀድሞ ወንድሞቹና እህቶቹን አርማ አንግቦ በመነሳት ቃል ኪዳኑን ማደስ ይኖርበታል እንጂ እንዳንተ እጅ መስጠት የለበትም ::

*« ይህ ትኩስ እንጀራ እንዴት ያስጎመጃል፤ ባደረ ቃሪያ ቢኮሸ ኩሹት ፤»* *ብለህ አልመህ ከሆነ እነዚህ ሰዎች እንኳን ትኩስ እንጀራ የሻገተውንም አያቀምሱህ:: በነገራችን ላይ በትምህረተ ጥቅስ ያስቀመጥኩት የምንኮራበት የአማርኛ ጥቅስ ወይም ምሳሌ እንጂ ተንኮል አይደለም:: ቅኔ ለመዝረፍ አልታደልኩም፤ በአገሬ ወግ በቄስ ት/ቤት ዳዊት ከመድገሜ በቀር: እድሉ ኖሮኝ እስከ ቅኔው አልዘለኩም፤ ብማረው ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር!*

*በዘረኝነት፤ በርሃብ፤ በበሽታና በፍርድ እጦት፤ የሚሰቃየው ወገንህ ትውስ ሳይልህ ከዚህ ዘረኛ ስርአት ጋር ለተባበሩና ቱባ ቱባ ለሚሸቱ ባለጊዜዎች ማንባትህ ባይገርም « ምርጫ በሌለው ምርጫ .....አረጋሽና ሰዬ እንዲያሸንፉ መርዳት...... በትግራይ ህዝብና በህወሃት ደጋፊዎች...ዘንድ ፍርሃት እንዳይኖር ያደርጋል »* *አልከን*

*ምነው እባክህ ወላድ በድባብ ትሂድ! ያለ እነሱ ሰው የለም ያለህ ማለው? ኢትዮጵያ የጀግኖችና የምሁራን ድሃ አይደለችም እነሱው ባመጡት የጎጥና የዘረኝነት ጣጣ እራሳቸውን በራሳቸው ይበላሉ፤ ኢትዮጵያም በጽኑ ልጆቿ ብርቱ ትግል ከወደቀችበት ትነሳለች::*

*« የምንመሰርተው አንድነት አንድነት የሚል ድርጅት፤ በርግጥ አንድነትን የሚያሳይ መሆን አለበት እንጂ ጠላት ነው ያሉትን ሁሉ ሊውጥ የተዘጋጀ የአማሮች ስብስብ » መምሰል የለበትም »*

*ምነው ልጅ ተክሌ? ጃስ! ያለህ ማነው? በመጀመሪያ አማራ፤ ኦሮሞ፤ ጉራጌ፤ ትግሬ፤ ወላይታ፤ ደርዜ፤......ወዘተ እያልኩ ወያኔ በመዘዘው የዘር ሃረግ እየተጠለፍኩ መደናበር አልሻም::*

*በአፄ ቲዎድሮስ ከተመሰረተቸው ኢትዮጵያ ጀምሮ አብዛኛው ወገናችን የዘር ሃረጉን ትቶ በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራ ጀግና ሕዝብ በመሆኑ መጠሪያውን የሰሜን ኢትዮጵያ፤ የደቡብ ኢትዮዮጵያ፤ የምሥራቅ፤ የምራብና የመሃል አገር ሰው: ይባባላል እንጂ: አንተ የለጠፍከውን « የሚጠቀሙት አንድም ሻዕቢያ ሁለትም ወያኔዎች ናቸው እንግዲህ የትኛው ጃስ! እንዳለህ አንተው ታውቃለህ::*

*ያሻህን መሆን መብትህ ነው: በ21ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ: በቃላት መግባባት ሰንችል: እንደ አህያ መራገጡን ምን አመጣው? ነው የኔ ጥያቄ ያውም በሰለጠነው ዓለም ብዙ የምንማርበት ቦታ እየኖርን ::*

*ለመሆኑ፤*

- *አማራ ሰንል ምን ማለታችን ነው?*
- *ምን አሉታዊ ስሜትስ አዝሎ ይጠራል?*
- *የዚህ ወገናችን ወግና ባህሎችስ ምን ይመስላሉ? ከሚለያዩን የሚያገናኙንስ አይበልጡም?*
- *ከአማራነቱስ ኢትዮጵያዊነቱን በማስቀደሙ ወንጀሉ ምንድነው?*
- *ዛሬ ባገራችን ማን ያልተቀሳቀለ ያልተካለሰ አለና በአንድ ወገናችን ላይ ካራ መዘን እንነሳለን?*
- *አማራ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ወገኖቻችንን ጨምሮ: በፈጸሙት ጀግንነት መመስገን ሲገባቸው: እንዲሸማቀቁ ለምን ተፈለገ? ....ወዘተ ብሎ ሳይጠይቁና በቂ መልስ ለማግኘት ሳያገላብጡ: ወይም ጠይቀው ሳይረዱ: ለጠላት ኮሶ፤ ለወገን ምሰሶ፤ የሆነው ወገናችን ለወዳጅ ሩህሩህ ከመሆኑ የተነሳ: መሸብኝ ቢሉ እግር አጥቦ፤ እራት አብልቶ፤ አልጋውን ትቶ የሚያስተናግድ ወገንን እንደ እባብ እራስ እራሱን መቀጥቀጥ ለምን አስፈለገ?*

  *ኧረ ጎበዝ እየተስተዋለ!*

  *እስቲ ቢቀፈኝም ለጊዜው በናንተው ቋንቋ ልጠቀም: እባካችሁ አንሳሳት ኢትዮጵያ አገራችን ያለ ኦሮሞው ወተትና ቂቤ፤ ያል ጉራጌው ክትፎና ቆጮ፤ ያለ አማራው ነጭ ጤፍና ጠላ፤ ያለትግሬው ሻይና አንባሻ፤ ያለደርዜው ጥበብ፤ ያለ ከፋው ቡና፤ ያለ ሲዳማው ቡናና ወርቅ፤ ያለጎንደሬው ማርና እስክስታ፤ ያለወላይታው ዳንኪራ፤ ያለ ሰላሌው ጎፈሬ፤ ያለ አደሬው ስፌት፤ ያለሱማሌው ጨት፤ያለ አፋሩ ግመል፤ ያለቦረናው ከብት...ወዘተ አገራችን ኢትዮጵያ አያምርባትም ከነዚህና ካልጠቀስኳቸው ልጆቿ አንዱ እንኳን ቢጎል በውብቷ ላይ እንከን ያመጣል እናም ሁላችንም ላገራችን እንቁዎች ነን በዚህም አገራችን ተውባ፤ ታፍራና ተከብራ ትኖራለች::*
  *አንዱ አንዱን አይግፋ! አንገፋፋ! አጉል አወዳደቅ እንዳንወድቅ!!*

  *« አረጋሽ አዳነ ጣይቱ ቡጡልን ብትሆንስ? »*

*በመሰረቱ አረጋሽ እራሷን እንኳን ብትጠይቃት ፡ ጣይቱ ቡጡልን መሆን እንደማትችል፡ እንደምትነግረህ አልጠራጠርም ፡፡ አቶ መለሰ ለትግራይ ሕዝብ የአፍ ጨማ ሲያቀርቡ « ከወርቅ የተፈጠርኩ » እንዳሉት ሁሉ አንተም ለአረጋሽ የአፍ ዝልዝል ይዘህ ለመቅደብ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ፋይዳ የለውም ፡፡ እንዳውም እተጌ ጣይቱ ቡጡል ፡ ያሉትን እንዳስታውስ አረከኝ፡ ከእምዬ ምኒልክ ሞት በኋላ ፡ እንጦጦ ማርያም አፋፉ ላይ ሆነው ፡ ያ ውሎት ! ያ ቤተ መንግሥቱ ነው ! ያ ደግሞ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ! እያለች ደንገጡራቸው ሲታሳያቸው « ነበር እንዲህ ቅርብ ነው !» አሉ ይባላል ፡፡*

*ነበር እንዲህ ቅርብ መሆኑን ፡ ፈጣሪ በሕይወት እያሉ እንዲታዘቡ ፡ ያደላቸው ውድ፣ እንቁ፣ ጀግና፣ ብልህ፣ ባለሞያና ያገር እናት ጣይቱ ወደር የላቸውም ፡፡ የማይወዳደሩ ሰብዕናዎችን ማወዳደር የታሪክ ዘረፋ ነው ፡፡*

*በአደዋ ጦርነት ወቅት ፡ እተጌ ጣይቱ እሳቸው ፡ በገዛ እጃቸው ሰርተው እየመግቡ የሚያዙት የጦር ሃይል ፡ በእሳቸው አዛዥነት ፡ የጣሊያን ጦር ውሃ ይቀዳበት የነበረውን የውሃ ጉድጓድ እንዲይዝ በማድረግ የጣሊያን ጦር እጁን እንዲሰጥ ያደርጉ ጀግና ንግሥት እንዲህ በዛሬ አፈ ጮሌ ክብራቸው በአሞሌ ጨው ሲለውጥ መስማቱ ያሳዝናል፣ ያስቆጫል፣ ያንገበግባል ም፡፡*

*« ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል » ነውና የቄሳርን ለቄሳር የእዚአብሔርን ለእግዚአብሔር እንስጥ እንጂ አናጨማልቅ ፡፡*

*ከዚህ በተረፈ በቀጣይነት የተባለው ፡ አልኩ ለማለት ያህል የተባለ በመሆኑ ፡ ጊዜዬን መቆጠብ መርጫለሁ ፡፡*

*ከዚሁ ጽሁፍ ጋር በተያያዘ ፡ ጥቂት አጋፋሪዎች ከዣንጥራር ጋር ለማዕድ ካራቸውን ይዘው መቅረባቸው ያሳዝናል ፡፡*

*ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !*

*እግዚአብሔር ኢትዮጵያና ሕዝቧን ይባርክ !!*

*ሚያዝያ 1 ቀን 2002 ዓ.ም* **(April 9/2010)**